የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ
ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር







# ዳያስፖራው ለሀገሩ

## በጤናው ዘርፍ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተሳትፎ



## ራዕይ

ጤናማ ፣ አምራችና የበለፀገ ህብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት ነው።

## ተልዕኮ

ከአጋሮቻችን ጋር በመተባበር የተማከለ ዲሞክራሲያዊና የተቀናጀ የጤና ማበልፀግ፣ በሽታ መከላከል፣ ህክምናን መልሶ ማቋቋም እንዲሁም የቁጥጥር ስርአት በመዘርጋት የሀገራችንን ህዝቦች ከበሽታ፣ ከሞትና ከአካል ጉዳተኝነት ማላቀቅ።

## እሴቶች

- የህብረተሰቡን ጥቅም ማስቀደም
- በትብብር መስራት
- ቁርጠኝነት
- ለለውጥ መስራት
- እምነት
- ቀጣይነት
- ሙያዊ ክህሎትን ማሳደግ

## ተቋማዊ ገጽታ

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አዲስ የአሰራር ለውጥ በመላ ሃገሪቱ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህ መሰረት የጤናው ዘርፍ ተቋማዊ ገጽታ በሚከተሉት ሶስት ዋና ዋና መዋቅሮች ላይ የተመሰረተ ነው።

- አገልግሎት ሰጪ
- አገልግሎት ገዢ
- የቁጥጥር አካል

አድራሻ፡- ልደታ ክ/ከ ቀበሌ 07/14 የቤት ቁጥር 056
ፖ.ሣ.ቁ 1234 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ 011 551 7011፣ 011 551 7831
ፋክስ 011 552 7033 ኢሜይል moh@ethionet.et
ድረ ገጽ www.moh.gov.et

# የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መልዕክት

Ministry of Health



ዶ/ር አሚር አማን

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ

ዳያስፖራን አስመልክቶ ሁሉም የሚሰራው ሥራ አለ፡፡ መንግስት በተቻለው አቅም በውጪ ሀገራት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ ሃገራቸው መጥተው በልማቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፡፡ ነገሮች ምንም ያህል የተመቻቹ ቢሆኑ ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ ይሆናል ማለት ግን አይደለም፡፡ እንደ መንግስት የምንችለውን እናደርጋለን፡፡ ብዙ የዳያስፖራ አባላት ችግሩን (ቻሌንጁን) አልፈው ገብተው ብዙ ለውጥ ያመጡ አሉ፣ የእኛንም አይን የከፈቱና ወደ ትልቅ ደረጃ እንድንደርስ የረዱን አሉ፡፡ ሌሎቹም የነሱን ፈለግ ተከትለው የራሳቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው ብለን እናምናለን፡፡

በጣም ብዙ ሀገሮች የለሙት (ያደጉት) የዳያስፖራው ተሳትፎ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ነው፡፡ በተለይም በማህበራዊ ዘርፍ በትምህርት እና ጤና ላይ የዳያስፖራው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው፡፡ የሰብአዊነትም ድርሻ ስላለው ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን እናምናለን፡፡ እኛ እንደ መንግስት ፖሊሲያችን ክፍት ነው፡፡ አገራቸው ነው ስለዚህ ሁሉም የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት አብረውን እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥረናል፡፡ እዚህ እኛ ሚኒስቴር መ\ቤት አብረውን እየሰሩ ያሉ በየክልሉም በበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ አሉ፡፡ ስለዚህ የነርሱን ፈለግ ተከትለው በጤናው ዘርፍ እንዲሁም በአጠቃላይ የሀገሪቱ የልማት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ በዚህ አጋጣሚ መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ አመሰግናለሁ!

# ዳያስፖራ ማነው?

Ministry of Health

ዳያስፖራ የሚለው ቃል አንድ ወጥ የሆነ እና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ድንጋጌ የለውም፡፡ ምክንያቱም ቃሉ ወይም ርዕሰ-ጉዳዩ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ የህዝብ ፍልሰቶችንና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ነውና፡፡ ስለዚህም የተለያየ ቅርፅና ይዘት ያላቸውን የዳያስፖራ ዓይነቶች ለጊዜው ትተን በዛሬው ዘመናዊ አለም ተደጋግሞ የሚጠቀሰውን የዳያስፖራ አይነት በአጭሩ እንመልከት፡፡

ዘመናዊ ዳያስፖራ የሚባሉት ከትውልድ ሀገራቸው ወጥተው በሌላ ሀገር የሚኖሩና የትውልድ ምንጫቸው (የአያት ቅደመ አያቶቻቸው) ሌላ ሀገር ሆኖ በልዩ ልዩ ምክንያት በሌላ ሁለተኛ ሀገር በቁጥር (ካረፉበት ሀገር ህዝብ) አነስ ብለው እንደ ሃገሬው የሚኖሩ፣ የራሳቸው ማንነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ከመጡበት ሃገር ወይም የዘር ግንዳቸው ከሚገኙበት (ከሚነሳበት) ሀገር ህዝብ ጋር የጠበቀ መንፈሳዊና ቁሳዊ ትስስር ያላቸው ናቸው፡፡ በሁለተኛ ሀገራቸው የሚኖራቸው ቆይታም ጊዜያዊ ወይም ዘለቄታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና ከትውልድ ሀገራቸው ወይም የዘር ግንዳቸው ከሚነሳበት ሀገር ጋር ያላቸው ጥብቅ ቁሳዊና መንፈሳዊ ትስስር ለልማት ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

## ኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራ አባላት የሚባሉት እነማን ናቸው?

- ኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራ አባላት በዜግነት ኢትዮጵያዊ ሆነው ነገር ግን ከትውልድ ሀገራቸው ከአንድ አመት በላይ ርቀው የኖሩ ናቸው፡፡

## ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የዳያስፖራ አባላት እነማን ናቸው?

- ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራ አባላት የሚባሉት በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው በዜግነት ደግሞ የሌላ ሀገር ዜጋ ሲሆኑ ነው፡፡






# በኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ የልማት ፕሮግራሞች

* የፌደራል የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ግቦች ምንድናቸው?

Ministry of Health

## የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሦስቱ ቁልፍ ተግባራት

1. የሕፃናትን ሞት መቀነስ
2. የእናቶችን ጤና ማሻሻልና የሞት መጠንን መቀነስ
3. የተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት በመከላከል መግታትና መቆጣጠር በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ፣ወባ ፣ሳንባ ነቀርሳና ሌሎች በሽታዎች የመያዝና የመሞት መጠንን መቀነስ ናቸው፡፡

## ከላይ በተጠቀሱት ሶስት ቁልፍ ተግባራት ምን አይነት ተጨባጭ ስኬቶች ተመዘገቡ?

1. የሕፃናትን ሞት በመቀነስ በኩል ቀደም ብሎ በታቀደው ዕቅድ መሰረት እ.ኤ.አ በ 2015 ዓ.ም የሕፃናትን ሞት በ2/3ኛ የመቀነስ ዕቅድ ኢትዮጵያ ቀደም ብላ በ 2013 /ሁለት ዓመት እየቀረው ማሳካት ችላለች፡፡
2. የእናቶችን ጤና በማሻሻል የሞት መጠንን በመቀነስ በኩል ኢትዮጵያ አበረታች ውጤቶችን አስመዝግባለች፡፡ ይኸውም እ.ኤ.አ በ 2013 ዓ.ም 69 በመቶ መቀነስ የቻለች ሲሆን በየዓመቱ 5 በመቶ ስለሚቀንስ እስከ 2015 ዓ.ም በሁለት ዓመቱ 10 በመቶ ሲቀንስ 79 በመቶ ይደርሳል፡፡ ይህም ከተያዘው 75 በመቶ በላይ ማለት ነው፡፡
3. ተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር የተመዘገበው ውጤትም አመርቂ ነው፡፡
    - በተለይ በኤች አይ ቪ/ኤድስ የመያዝ መጠንን ቀድሞ ከነበረበት አንፃር 90 በመቶ መቀነስ ተችሏል፡፡ ይህም በሚሊኒየሙ የልማት ግቦች ከተያዘውም ሆነ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዕቅድ በላይ የተገኘ ውጤት ነው፡፡
    - በሳንባ ነቀርሳ፣በወባና በሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች ደግሞ በበሽታዎች የመያዝም ሆነ የመሞት መጠን ከ60 በመቶ በላይ መቀነስ ተችሏል፡፡
    - በዘርፉ የተገኘው ውጤት ሕዝብን ጤናማና አምራች እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፆኦ አድርጓል፡፡







# በጤናው ዘርፍ ባለፉት 20 ዓመታት የተመዘገቡት አስገራሚ ለውጦች

Ministry of Health

* ከ1983 ዓ.ም በፊት 125 የጤና ተቋማት ብቻ ነበሩ አሁን ከ 3,400 በላይ የጤና ተቋማት አሉ።
* የሕክምና ትምህርት የሚሰጡ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል።
* የሐኪሞች ቁጥር በጣም እየጨመረ ነው።
* ተደራሽነት እና አጠቃላይ የጤና ሽፋን በከተማም በገጠርም በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል።

## ዋና ተግዳሮቶች /ክፍተቶች/ እና ቀጣይ ስራዎች

* የጤና ተቋማት ጥራትን ማሻሻል
* የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሳደግ
* የጤና ባለሞያዎች ጥራትን ማሻሻል ናቸው





የፖሊሲ ሰነዱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ መንግስት የዳያስፖራ ፖሊሲ በመባል ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፖሊሲ ሰነድ ቀድሞ ይሰራባቸው የነበሩ መመሪያዎችን በዝርዝር ፈትሿል፡፡ የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን በግብዓትነት አካቷል፣ ልዩ ልዩ ተሞክሮዎችን ወስዷል፣ የሌሎች ሀገሮችን ጠቃሚ ልምዶች በግብዓትነት ተጠቅሟል፤ በኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት የተሰጡ አስተያየቶችን አካቷል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላትን ተሳትፎ ለማሳደግ፣መብትና ጥቅማ ጥቅማቸውን የማስከበር ስልጣንና ኃላፊነት ለውጪ ጉዳይ ሚኒስተር ሰጥቶታል፡፡

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት በስሩ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬትን አቋቁሟል ፡፡
- በውጭ ጉዳይ ሚኔስቴር ስር የሚገኘው የዳያስፖራ ጉዳዩች ዳይሬክቶሬት ሰፊ አደረጃጀት ያለው ሲሆን በሌሎች ትላልቅ የመንግስት ተቋማት፣ የአስተዳደር ክልሎች እና ከተሞች የዳያስፖራ ጉዳዮች ጽ/ቤቶች እንዲቋቋሙ አድርጓል፡፡
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ሆነ የዳያስፖራ ጉዳዩች ዳይሬክቶሬት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፋፊ ውጤታማ ስራዎችን ሰርተዋል፡፡
- የዳያስፖራ ዳይሬክቶሬት በርካታ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገር ቤት መዋለንዋያቸውን እንዲያፈሱ አስችሏል፡፡
- እውቀት እና ክህሎታቻውን ለአገራቸው ጥቅም እንዲያውሉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን እንዲያግዙ ድጋፍ ሰጥቷል፡፡ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ በመላክ ንግድ እና ቱሪዝምን በማስፋፋት፣ የሀገሪቱን ገፅታ በመገንባት በኩል የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ተሳትፎ እንዲጎለብት የዳያስፖራ ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት በሀገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አግዟል፡፡
- ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሀገር ቤት ኢንቨስት ለማድረግ ሲፈልጉ ማሟላት የሚጠበቅባቸውን መመዘኛዎች እና መስፈርቶች በዝርዝር ያስተዋውቃል፡፡
- የኢትዮጵያ የዳያስፖራ አባላት ማህበር እንዲቋቋም አበረታቷል፡፡ ዓመታዊ የኢትዩጵያ ዳያስፖራ ቀን (በዓልን) እንዲያከብሩ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

# በጤናው ዘርፍ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ተሳትፎ



በጤናው ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት መንግስት አስፈላጊውን ሁኔታ ሁሉ አመቻችቷል፡፡ በዚህም መሰረት በተለያዩ የጤና ስራዎችና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የተሰማሩ ወደ አንድ ሺህ ሰባት መቶ /1700/ የሚሆኑ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላትን ማፍራት ተችሏል፡፡

## በጤናው ዘርፍ የተሰማሩት ባለሀብቶች እና የጤና ሞያተኞች ማዕከላት ዓይነት

- አጠቃላይ እና ልዩ (special) ክሊኒኮች
- አጠቃላይ እና ልዩ (special) ሆስፒታሎች
- ክሊኒካል ላብራቶሪዎች
- የምርመራ (ዲያግኖስቲክ) ማዕከላት
- መድሀኒት አስመጭና አምራች ማዕከላት
- የህክምና መርጃ መሳሪያዎችን አስመጪና አምራች ማዕከላት
- የህክምና ትምህርት የሚሰጡ የስልጠና ማዕከላት እና ኮሌጆች ይገኙባቸዋል፡፡






ዶ/ር ፈቀደ መንግስቱ

**የአይን ህክምና ጥንቃቄ ማዕከል** በዶ/ር ፈቀደ መንግስቱ መስራችነት እና ባለቤትነት የተቋቋመ ነው፡፡ ዶ/ር ፈቀደ በዓይን ህክምና ስራ ከ 30 ዓመታት በላይ ቆይተዋል፡፡ የመጀመሪያ የህክምና ዲግሪያቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ የተማሩ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን (ድህረ ምረቃ) ትምህርታቸውን እስራኤል አገር ነው የተማሩት፡፡ የተሻለ ክፍያ እና የሞያ እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሀገረ እስራኤልን ትተው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል፡፡ሀገሬን ወገኔን ባግዝ ይሻላል ብለው ማለት ነው፡፡ እርሳቸው በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ወደ ሀገር ቤት ሲመለሱ በኢትዮጵያ የነበሩት የዓይን ህክምና ስፔሻሊስቶች 3 ብቻ ነበሩ፡፡ እርሳቸው አራተኛ ሆነው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ በተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የጤና ተቋማት ውስጥ የወገናቸውን ዓይን እያከሙ ቆይተዋል፡፡ በሀገሪቱ አራቱም ማዕዘናት እየተጓዙ በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የዓይን ህሙማንን አክመዋል፡፡ የያኔው ውሳኔያቸው ለብዙ ኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራ ሀኪሞች አርአያ ሆኗል፡፡

**ሳህለ ስላሴ አርአያ ከፍተኛ የጥርስ ህክምና ክኒሊክ፣** በዶ/ር ሳህለ ስላሴ መስራችነት እና ባለቤትነት የተቋቋመ ነው፡፡ ዶ/ር ሳህለ ስላሴ የጥርስ ህክምናን በዩ.ኤስ. አሜሪካ ነው የተማሩት፡፡ እዚያው አሜሪካን ሀገር ከ25 ዓመት በላይ ኖረዋል፡፡ በራሳቸው ክሊኒክ ውስጥም ሰርተዋል፡፡ ሆኖም ከ25 ዓመታት የአሜሪካ ቆይታ በኋላ የሀገር ፍቅር እና ወገንን የማገልገል ዕት እምነት ስለነበራቸው መንግስት ለኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ያመቻቸውን ዕድል ተጠቅመው ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ በሙያቸውም ከፍተኛ ከበሬታን አትርፈዋል፡፡ ዶ/ር ሳህለ ስላሴ የጥርስ ህክምናን በሀገሪቱ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሌላ ተጨማሪ የስልጠና ማዕከልም አቋቁመዋል፡፡ ማዕከሉ እንደ መማሪያ እና የስልጠና ተቋምም ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሳህለ ስላሴ አርአያ የጥርስ ህክምና ማዕከል ለብዙዎች የስራ ዕድል ከፍቷል፡፡ ተቋሙ ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ የውጭ ሀገራት የጥርስ ህክምና ስፔሻሊስቶችንም ቀጥሮ እያሰራ ይገኛል ፡፡


ዶ/ር ሳህለ ስላሴ አርአያ

**ፈርስት ካይሮፕራክቲክ ክሊኒክ** በዶ/ር ሰላም አክሊሉ መስራችነት እና ባለቤትነት የተቋቋመ ነው፡፡ ዶ/ር ሰላም አክሊሉ የህክምና ሙያን ሰሜን አሜሪካ ነው የተማሩት፡፡ እዚያው አሜሪካን ሀገር ከ 27 ዓመታት በላይ ኖረዋል፡፡ 13 ዓመታት ያህል ደግሞ እዚያው ዩ.ኤስ አሜሪካ ውስጥ የግል ክሊኒክ ከፍተው ሰርተዋል፡፡ መንግስት ለኢትዮጵያ ዳያስፖራ ሐኪሞች ያመቻቸውን ዕድል ተጠቅመው ወደ ሀገር ቤት ተመለሱ፡፡ ክሊኒካቸውን ባቋቋሙ በአጭር ጊዜ ውስጥም ተፈላጊ ሀኪም ሆኑ፡፡ ወገንን በህክምና ስራ ከመርዳት ውጪ ሀገር ከሚገኘው ገንዘብ በላይ እርካታው ልዩ ነው ይላሉ፡፡



ዶ/ር ሰላም አክሊሉ



ዶ/ር ቴድሮስ መሰሰ

**ዶ/ር ቴዎድሮስ መሰለ** ህክምና ሙያን በዩ ኤስ አሜሪካ ነው የተማሩት፡፡ እዚያው አሜሪካም ለበርካታ ዓመታት ሰርተዋል፡፡ የተማሩት የሰርጀሪ ህክምናን ነው፡፡ ይህንን ህክምና ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገባ ለማስተዋወቅ ፅኑ ፍላጎት ነበራቸው፡፡ የባዕድ አገር ኑሮም በቃኝ ብለው መጡ፡፡ እንግዳ ከመሆን ጋር ተያይዞ ያጋጠማቸውን ሁሉ አልፈው ክሊኒካቸውን ከፈቱ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥም ዝነኛና በሙያቸው ተፈላጊ ሐኪም ሆኑ፡፡ በውጭ ሀገራት ያሉ ኢትዮጵያውያን የሙያ ባልደረቦቻቸው ወደ ሀገር ቤት ቢመለሱ ብዙ የሚሰራ ስራ አለ ይላሉ፡፡

**ተስፋ ማርያም ከፍተኛ ክሊኒክ** በዶ/ር መስፍን ተስፋዬ መስራችነት እና ባለቤትነት የተቋቋመ ነው፡፡ ዶ/ር መስፍን የህክምና ትምህርታቸውን የተማሩት በዩ ኤስ አሜሪካ ነው፡፡ መንግስት ለኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ያመቻቸውን ዕድልም ተጠቀሙ እናም በጊዜው ክሊኒኩን ለማቋቋም ያጋጠማቸውን ውጣ ውረድ ሁሉ አልፈው ሀሳባቸውን እውን አደረጉ በአጭር ጊዜ ውስጥም በሙያቸው ተፈላጊ ሐኪም ሆኑ ፡፡



ዶ/ር መስፍን ተስፋዬ

**መርሴት ከፍተኛ ዲያጎኖስቲክ ክሊኒክ** በዶ/ር ዘውዱ ተፈጠርቀ መስራችነት እና ባለቤትነት የተቋቋመ ነው። ዶ/ር ዘውዱ የህክምና ትምህርታቸውን በዩ ኤስ አሜሪካ ነው የተማሩት በተለያዩ ሀገራትም እየተዘዋወሩ ሰርተዋል። በሰሩባቸው ሀገራትም በጣም ተፈላጊ እና ዝነኛ ሆነዋል። ልዩ ስልጠና (ስፔሻላይዝ ባደረጉበት) የዴያግኖስቲክ ህክምና ስራ ሀገራቸውን ለማገልገል ወስነው መጡ። መንግስት ያመቻቸውን ዕድል ተጠቅመው ለረጅም ጊዜ ሲያልሙት የነበረውን የዲያግኖስቲክ ህክምና ማዕከልን በአገራቸው አቋቋሙ። ቀድሞ ለDNA እና መሰል ውድ የምርመራ ስራ የደም ናሙና ወደ ውጭ ሀገራት ይላክ የነበረውን ረጅም መንገድ አሳጥረው አዲስ አበባ አመጡት። ዛሬ ክሊኒኮች እና የሀገሪቱ ትላልቅ ሆስፒታሎች ጭምር የማዕከሉ ደንበኞች ናቸው።


በዶ/ር ዘውዱ ተፈጠርቀ


አቶ ታምራት በቀለ

**ኢንተርናሽናል ክሊኒካል ላብራቶሪ** አደረጃጀቱ ሰፋ ያለ እና ለበርካታ ሰራተኞች የስራ እድል የከፈተ ነው። ማዕከሉ በዓለም አቀፍ ካምፓኒዎች የበጀት ድጋፍ የተቋቋመ ትልቅ የህክምና ማዕከል ነው። ከመስራቾቹ አንዱ እና ስራ አስኪያጁ አቶ ታምራት በቀለ ናቸው። አቶ ታምራት በውጭ ሀገራት ነው የህክምና ሙያን የተማሩት። አቶ ታምራት እና የሙያ አጋሮቻቸው ይህን ማዕከል ለማቋቋም የትላልቅ አለም አቀፍ ተቋማትን የበጀት ድጋፍ ለማግኘት ብዙ ታግለዋል። በመጨረሻም ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ትልቅ ተቋም የማቋቋም ውጥናቸውን ዕውን አድርገዋል። ማዕከሉ በዋናነት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ለሆስፒታሎች እና ለአለም አቀፍ ተቋማት ነው። በ10 ዓመታት የስኬት ጉዞው እና የጥራት ደረጃው በሀገር አቀፍ ደረጃ ተሸላሚ ሆኗል። ማዕከሉ በሀገሪቱ ዋና ዋና ቦታዎች ቅርንጫፍ ማዕከላትንም እየከፈተ ይገኛል። በደቡብ ሱዳንና ፑንት ላንድ መሰል ተቋም ለማቋቋም በማዕከሉ ዕቅድ ተይዟል። አቶ ታምራት ለኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት በሀገር ቤት የተመቻቸውን ዕድል እንዲጠቀሙበት እንዲሁም ለስራ ሲመጡ ፅናት እንዲኖራቸው ይመክራሉ ።



ዶ/ር መኮንን ሐጎስ

**ሚድኮ ባዮ ሜድካል ኮሌጅ** በኢትዮጵያዊ ዳያስፖራ አባል የተከፈተ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የግል የጤና ኮሌጅ ነው፡፡ ለብዙ የግል የጤና ኮሌጆች መከፈት ፈር ቀዳጅ በመሆን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ የሚድኮ ባዮ ሜድካል ኮሌጅ መስራችና ባለቤት ዶ/ር መኮንን ሐጎስ ናቸው፡፡ ዶ/ር መኮንን የህክምና ትምህርታቸውን በስዊዲን እና በዩ ኤስ አሜሪካ ተከታትለዋል፡፡ በአሜሪካና በተለያዩ የአውሮፓ ሐገራት ለ21 ዓመታት በተለይም በመድሀኒት ግኝትና ምርምር ስራ ላይ ብዙ እንደሰሩ ይናገራሉ፡፡ በጊዜው የግል የጤና ኮሌጅ አለመኖሩን ካረጋገጡ በኋላ የመንግስትን የፖሊሲ ሰነዶች ፈተሹ፡፡ አዋጭነቱንም ካጠኑ በኃላ ስራውን ጀመሩ፡፡ ሆኖም ከስራው አዲስነት ጋር ያጋጠማቸውን ውጣ ውረዶች ሁሉ አልፈው ውጥናቸውን እውን አድርገዋል፡፡ ሚድኮ ባዮ ሜድካል ኮሌጅ ለበርካታ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች የስራ ዕድልን ፈጥሯል፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ የጤና ባለሞያዎችን በማፍራትም በሀገሪቱ የጤና እና የህክምና አገልግሎት ስራ ውስጥ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

**ኒዮ ባዮ - ሜድካል ኢንጅነሪንግ** መለስተኛ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ማዕከሉ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን ያመርታል ይጠግናል፡፡ የውጭ ስሪቶችንም ይገጣጥማል፡፡ የኒዮ ባዮ-ሜድካል ኢንጅነሪንግ ተቋም (ኢንዱስትሪ) መስራችና ባለቤት አቶ ነጋ ከበደ ናቸው፡፡ አቶ ነጋ በዩኤስ አሜሪካ ለ15 ዓመታት ኖረዋል፡፡ የባዮ ሜዲካል ኢንጅነሪንግ ትምህርታቸውን እዚያው ዩ.ኤስ አሜሪካ ነው የተከታተሉት፡፡ በተለያዩ ተቋማትና ሆስፒታሎች ውስጥ በሙያቸው አገልግለዋል፡፡ ሆኖም መንግስት በሀገር ቤት ለኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ያመቻቸውን ዕድል ተጠቅመው በዘርፉ (በባዮ-ሜዲካል ኢንጂነሪንግ) ያለውን ክፍተት ተመልክተው ዝም አላሉም፡፡ ሞያቸውን ይዘው መጡ፡፡ በጊዜው በየሆስፒታሉ የነበረውን የህክምና መርጃ መሳሪያዎች አያያዝ ተመልክተው በቁጭት ስራውን ጀመሩት፡፡ ይሁንና በሀገር ቤት ከሙያው አዲስነት ጋር ተያይዞ ያጋጠማቸውን ውጣ ውረድ ሁሉ አልፈው ውጥናቸውን አሳኩ፡፡ ዛሬ የህክምና መሳሪያዎች በማምረት፣ መጠገንና መገጣጠም በኩል ኢንዱስትሪያቸው ተጠቃሽ ሆኗል፡፡ ከውጭም ሀገራት በውድ ዋጋ ተገዝተው ይመጡ የነበሩ አንዳንድ የህክምና መርጃ መሳሪያዎችን እዚሁ እንዲመረቱ አስችለዋል፡፡ ውድ ዋጋ ይወጣባቸውና በቀላሉ ሲበላሹ አስታዋሽ ያጡ የነበሩ የህክምና መርጃ መሳሪያዎች በተቋሙ ይጠገኑና አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡



አቶ ነጋ ከበደ

- አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከ 25 - 30% የአፍሪካ ምሁራን አውሮፓና አሜሪካ ውስጥ ይኖራሉ።
- በዓመት ከ 20 - 30 ሺህ ምሁራን ከድሃ አገሮች በኢንዱስትሪ ወደ በለፀገው አውሮፓና አሜሪካ አህጉር ይጎርፋሉ።
- በልዩ ልዩ ምክንያት ከሀገራቸው ወጥተው በአውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ከሚገኙት ኢትዮጵያውን ውስጥ ከ 30-40% የሚሆኑት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት የተማሩና ከዚያም በላይ ያጠናቀቁ ናቸው።
- እንደ አለም አቀፍ የጤና ድርጅት (World Health Organization) ጥናት መሰረት 175 ሚሊዮን ሕዝብ ማለትም ከዓለም ህዝብ 2.9% የሚሆነው ከትውልድ ሀገሩ ወጥቶ የሚኖር ነው።
- ከዚህ ውስጥ 65 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ ደግሞ በኢኮኖሚ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ነው።

## የጤና ባለሞያዎች ከሀገር ወደ ሀገር የሚያደርጉት ሽግግር

- የጤና ባለሞያዎች ከሌሎች የሞያ ዘርፎች በተለየ መልኩ ከሀገር ሀገር ይፈልሳሉ (ይሸጋገራሉ)።
- በርካታ ባለሞያዎች አፍሪካን ጥለዋት የመሄዳቸውን ያህል ደግሞ አህጉሪቱ በልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎች ማለትም በኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ ወባ፣ሳምባ ነቀርሳና ሌሎችም በሽታዎች ትሰቃያለች።
- አፍሪካውያን የሚሰቃዩባቸው የበሽታ አይነቶች በቀላሉ በቁጥጥር ስር የሚውሉ ቢሆኑም በጤና ሞያተኞች እጥረት ችግሩ አሁንም በከፋ ሁኔታ ላይ ይገኛል።

## ከአህጉሪቱ የወጡ የጤና ባለሞያዎችን የመመለስ ሂደት

- የአፍሪካ መንግስታት ለጤና ባለሞያዎች ከወትሮው በተለየ ማበረታቻ እያደረጉ ይገኛሉ። ከአህጉሪቱ የወጣውን የተማረ ኃይል ለመመለስም (From Brain Drain to Brain Gain) በሚል መርህ እየተንቀሳቀሱ ናቸው።
- የአፍሪካውያን ዳያስፖራ የጤና ባለሞያዎች ፊታቸውን ወደ ትውልድ ሀገራቸው እንዲመልሱ የሚያስችሉ ስልቶችን መንግስታቱ ነድፈዋል።
- በጤናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትን በማስተሳሰር አፍሪካውያን የዳያስፖራ አባላት በሀገራቸው የጤና ዘርፍ ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማስቻል አንዱ ስራ ነው።
- ለጤና ባለሞያዎች የፖሊሲ ድጋፍ በማድረግ ቀድሞ የተዘነጉ የስራ ዕድሎችንና ተጠቃሚነትን ማሳደግ አንዱ ስልት ነው ።
- ምርጥ የህክምና ስራ ተሞክሮዎችን መለዋወጥ እና ማሳደግ ሌላው የዳያስፖራ አባላት አብይ ተግባር ነው።
- በትውልድ የሌላ ሀገር ተወላጅ የሆኑ የአፍሪካ ወዳጆች ለህክምና ዕርዳታ እንዲሁም ለዕውቀትና ክህሎት ለውጥ እንዲያመጡ ማበረታታትና ድጋፍ ማድረግ ይገኝባቸዋል።

# የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት በዕውቀትና ክህሎት ሽግግር

**ኢትዩጱያውያን የዳያስፖራ አባላት በጤናው ዘርፍ በዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ሰፊ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡**

ብዙ ተቋማት የተለያየ ፕሮግራሞችን ቀርፀው ኢትዩጱያውያን ዳያስፖራ የጤና ባለሙያዎችን በበጎ ፍቃደኝነት በሀገር ቤት አገልግሎት እንዲሰጡ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ተቋማት አንዱ የአሜሪካን አለም አቀፍ የጤና ትብብር (American International Health Alliance /Twinning Center-Ethiopia) ነው፡፡ ተቋሙ ከ 1998 ዓ.ም ጀምሮ ኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በጤናው ዘርፍ የተማረ የሰው ሃይልን ረዘም ላለ ጊዜ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ በተጨማሪም በመላው ሃገሪቱ የቴክኒክ ድጋፍ እና አቅጣጫን በማመላከት የተቋማትንና የሰው ኃይል ብቃትን ዘላቂ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## በዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ዘርፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሚና

**የአሜሪካን አለም አቀፍ የጤና ትብብር ትዊኒንግ ሴንተር እና የጤና እንክብካቤ በጎ ፍቃደኛ ቡድን በኢትዩጱያ**

(Volunteer Healthcare Corps in Ethiopia)

- ተቋሙ በአሁኑ ጊዜ በኢትዩጱያ ሰባት የአቅም ግንባታ ጥምረት ስምምነት በተጨማሪ እጅግ ውጤታማ የጤና እንክብካቤ የበጎ ፍቃደኛ ቡድን የኢትዩጱያውያንን ጤና በዳያስፖራ በሚል ተነሳሽነት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡
- ተቋሙ ከኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ፕሮግራሞች በተገቢው ሁኔታ በመቅረፅና በመተግበር ከሀገሪቱ ስትራቴጂና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት አብሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡
- የተቋማትን ጥምረት የአሜሪካን አለም አቀፍ የጤና ትብብር ዘላቂ የሆነ የዕውቀት፣ ክህሎትና የልምድ ሽግግርን አብሮት ከሚሰሩ ተቋም ጋር (ለምሳሌ ዩኒቨርስቲዎችን፣ ሆስፒታሎችን፣ ክሊኒኮችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎችም) በኢትዩጱያና በአሜሪካ ያጣምራል፡፡
- የአሜሪካን አለም አቀፍ የጤና ትብብር ከዋና ዓላማዎቹ አንዱ በኢትዩጱያም ሆነ በሌሎች ሀገራት የወጣውን ዕውቀትና ክህሎት ወደ ሀገር ቤት እንዲመለስ ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ ይህንንም ከግብ ለማድረስ ዳያስፖራው ያካበተውን ዕውቀትና ክህሎት የኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራባቸው ያሉትን ሁኔታዎች በተገቢው ሁኔታ መደገፍ አንዱ ስትራቴጂ ነው፡፡

# የአሜሪካን አለም አቀፍ የጤና ትብብር ጥምረት

ተቋሙ ከ 1998 ጀምሮ የጤና ሲስተም ድጋፍ ጥምረት በኢትዩጵያ እያካሄደ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ያህል

• ደብረ ብርሃን ሪፈራል ሆስፒታል እና ኤልመረስት ሆስፒታል ሴንተር (ነውዩርክ) ፡- ይህ ትብብር ደብረብርሃን ሪፈራል ሆስፒታል በአደረጃጀቱም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱ በሀገሪቱ ሞዴል ሆስፒታል ሆኖ ብቅ እንዲል አስችሎታል፡፡

• አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ሜዲስን እና ዊስኮንሲን ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ሜዲሰን (ማዲሰን)፡- ይህ ትብብር የህጻናትና የአዋቂዎች የድንገተኛ ህክምና ትምህርትና ልምድን በመጀመር ፈር ቀዳጅ ነው፡፡ በዚህ ትብብር ተጨማሪ ስፔሺያሊቲ ስልጠና ለሀኪሞችና ነርሶች ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የዚህ ዓይነት ስልጠና መኖር ኢትዮጵያን በአፍሪካ ሶስተኛ ያረጋታል፡፡

• ጂማ ዩኒቨርስቲ ኢንስቲትዩ ኦፍ ቴክኖሎጂና ተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ራይስ ዩኒቨርስቲ እና ቴክሳስ የልጆች ሆስፒታል (ሂውስተን)፡- ይህ ትብብር ኢትዩጵያዊ ተባባሪ ተቋም በሀገሪቱ ሞዴል የሆነ የስልጠና አቅርቦት ለ ባዮሜዲካል ኢንጂነሪንግ እና ቴክኖሎጂ ሆኖ እንዲጠራ ቴክኒካል ድጋፍ ይሰጣል፡፡

• አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ፋርማሲ እና ሀዋርድ ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ፋርማሲ (ዋሽንግተን ዲሲ)፡- ይህ ትብብር የተቀረፀው የፋርማሲ ትምህርትና ተግባርን ለመላው ሀገሪቱ ለማዳረስ ነው፡፡ በዋነኝነት ፋርማሲስቶች ከሀኪሞች ጋር በመቀናጀት ለታማሚው ከፍተኛ አገልግሎት እንዲሰጡ ያግዛል፡፡

## የአሜሪካን ዓለምአቀፍ የጤና ትብብር ለዳያስፖራው የሚሰጠው ድጋፍ

• አሜሪካን አለም አቀፍ የጤና ትብብር ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ዋና መስሪያ ቤቱም ዋሽንግተን ዲሲ ይገኛል፡፡ በኢትዩጵያም በአዲስ አበባ ቢሮ አለው፡፡

• ይህ ቢሮ በጎ ፍቃደኞችን በተለይም የተማሩ ኢትዩጵያውያን ባለሙያዎችን ይመለምላል፡፡ በጎ ፍቃደኞችንም ከሶስት ወር እስከ ሁለት አመታት በመላው ሃገሪቱ በመመደብ ሀገር ውስጥ ካሉ ባለሙያዎች ጋር አብረው በመስራት የሚያስፈልጓቸውን የአቅም ግንባታ በመፈተሽ የእውቀትና ክህሎት ሽግግሩን ያካሂዳሉ፡፡

• መስሪያ ቤቱ የአለም አቀፍ አንዳንዴም ሃገር ውስጥ ትራንስፖርት፣ የቤት ኪራይ እና ተመጣጣኝ የመኖሪያ አበል በሀገር ውስጥ ይሸፍናል፡፡

**የአሜሪካን አለም አቀፍ የጤና ትብብር ትዊኒንግ ሴንተር ለኢትዩጰያውያን ዳያስፖራና ለኢትዩጰያ ወዳጆች በዚሁ አጋጣሚ ጥሪውን በማቅረብ ስለ ተቋሙ በማወቅ የኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስተር ያስጀመረውን የተሻለ ጤና በኢትዩጰያ መርህ ተሳታፊ ለመሆን ለምትፈልጉት መረጃ ለመስጠት በራችን ክፍት መሆኑን እንገልጻለን፡፡**

## አሊያንስ ፎር ብሬን ጌይን ኤንድ ኢኖቬቲቭ ዴቨሎፕመንት ኢትዮጵያ (ABIDE)

- መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፡፡
- ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጥምረት ይሰራል፡፡
- በውጭ ሀገራት ያለውን ዕውቀትና ክህሎት ወደ ሀገር ቤት እንዲመጣ ተቋማትን ከተቋማት እንዲሁም ሙያተኞችን ከተቋማት ጋር ያገናኛል ያስተሳስራል፡፡
- በሀገር ውስጥ ያለውን የጤና ባለሙያዎች የፍላጎት መጠን ያጠናል፡፡
- ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በቅርብ ይሰራል፡፡
- ኢትዮጵያ ውስጥ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ሙያዊ እገዛ እያደረገም ይገኛል፡፡

## ቮለንተሪ ሰርቪስ ኦቨርሲስ ኢትዮጵያ (VSO-E) በጤናው ዘርፍ ያለው ድጋፍ

- መንግስታዊ ያልሆነ አለም አቀፍ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሲሆን በኢትዮጵያ ዋና ስራው የትምህርትና የጤናን ዘርፍ በማገዝ ድህነትን መቀነስ ነው፡፡
- “ክህሎትን ማጋራት ህይወትን መቀየር ” በሚል መሪ ቃሉ ይታወቃል፡፡
- በጤናና በትምህርት መስክ የተሰማሩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ባለሙያዎችን ከመላው ዓለም እየመለመለ ወደ ኢትዮጵያ ያመጣል፡፡
- በበጎ ፍቃድ አገልግሎት መሰማራት የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ-ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በብዛት ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡና ዕውቀትና ክህሎታቸውን እንዲያካፍሉ ሰፊ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡
- ካናዳ የሚገኘው ዋናው ፅ/ቤት የበጎ ፍቃደኞቹን መልምሎ ወደ ኢትዮጵያ ይልካል፡፡
- ተቋሙ በጤና እና በትምህርት ዘርፍ ኢትዮጵያውያንን ማገልገል እንፈልጋለን የሚሉና በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ የኢትዮጵያ ወዳጆችን ለማስተናገድ በሩ ክፍት ነው፡፡

# የኢትዮጵያውያ በጎ ፈቃደኞች የዳያስፖራ አባላት ተሳትፎ



ዶ/ር ፍፌው ስማ

**ዶ/ር ፍፌው ስማ፡-** የህክምና ባለሙያ ናቸው፡፡ በውጪ ሀገራት በትምህርትና በስራ አለም ለዓመታት ኖረዋል፡፡ አሁን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚኒስትሩ ቢሮ በከፍተኛ ደረጃ አማካሪ ናቸው፡፡ በተለይ በሥርዓተ-ምግብ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረጻ እና አፈጻጸም ክትትል ላይ ይሰራሉ፡፡ ለሶስት ወራት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የመጡ ቢሆንም ለ4ኛ ዓመት ቆይታቸውን አራዝመዋል፡፡ አገራቸውን በማገልገላቸውም በጣም ደስተኛ ናቸው፡፡ ሌሎች በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የጤና ባለሙያዎች ለአጭር ጊዜም ቢሆን መጥተው ሀገራቸውን በበጎ ፈቃደኝነት እንዲያገለግሉ ይመክራሉ፡፡

**ዶ/ር ወንድወሰን እሸቱ፡-** የህክምና ባለሞያ ናቸው፡፡ በተለያዩ ሀገሮችና አለም አቀፍ የህክምና ድርጅቶች ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት ሰርተዋል፡፡ አሁን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አማካሪ ሲሆኑ በኢትዮጵያ የተለያዩ የህክምና ትምህርት የሚሰጡ ዩኒቨርስቲዎችንም ያማክራሉ፡፡ ዶ/ር ወንድወሰን ጠቅለው ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ በመመለሳቸውም በጣም ደስተኛ ናቸው፡፡ ወገንን በዚህ ሞያ ማገልገል ትልቅ ደስታ ይሰጣል እናም ሌሎች ዳያስፖራ የጤና ባለሞያዎች ወደ ሀገራቸው በተቻለ አቅም ቢመጡ እርካታውን አይችሉትም ይላሉ፡፡



ዶ/ር ወንድወሰን እሸቱ

**ወ/ሮ ኮከብ ብርሃኑ፡-** የኮምፕዩተር ኢንፎርሜሽን ሲስተም ባለሞያና የፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን (የህዝብ አስተዳደር እና የፖሊስ ጥናት) ባለሞያም ናቸው፡፡ በዩኤስ አሜሪካ በትምህርትና በሥራ ዓለም ለአስራ አራት አመታት ቆይተዋል፡፡ ሀገራቸውን በበጎ ፈቃደኝነት ለአጭር ጊዜ ለማገልገል መጥተው መኖሪያቸውን እዚሁ አድርገዋል፡፡ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በፌደራል ኤች አይቪ /ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በበጎ ፈቃደኝነት አገልግለዋል፡፡ በመንግስት ተቋማት ውስጥ መስራታቸው ትልቅ እውቀትና እርካታ እንዳስገኘላቸው ይናገራሉ፡፡




ወ/ሮ ኮከብ ብርሃኑ



ወ/ሮ ሰብለ ነብዩልዑል

**ወ/ሮ ሰብለ ነብዩልዑል፡-** ሞያቸው የጤና ማዕከላት አመራርና አስተዳደር ነው፡፡ በአሜሪካን ሀገር የልዩ ልዩ የሆስፒታሎች አስተዳደሪ ሆነው ሰርተዋል፡፡ እዚያው አሜሪካን ሀገር ከ28 ዓመታት በላይ ኖረዋል፡፡ ከጥቂት አመታት ወዲህ ደግሞ ወደ ኢትዮጰያ በመምጣት በበጎ ፈቃደኝነት ሀገራቸውን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ በተለይም በጨቅላ ህፃናት ጤና እንክብካቤ ላይ ብዙ ሰርተዋል፡፡ በዚህም በጣም ትልቅ እርካታ አላቸው፡፡ ድርጅታቸው ኢንተርናሽናል ፈንድ ፎር አፍሪካ ለሆስፒታሎች የህክምና መሣሪያ በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፡፡





መምህር ያሲን ሩጅሉ

**መምህር ያሲን ሩጅሉ፡-** በሞያ የሕዘብ ግንኙነት እና የቢዝነስ አስተዳደር ባለሞያ ናቸው፡፡ አልባሳር ኢንተርናሽናል ፋውንዴሽን በተሰኘው ድርጀታቸው አማካኝነት የኢትዮጵያ ወዳጅ ሐኪሞችን ከልዩ ልዩ ሀገራት በማምጣት ህክምና እንዲሰጡ ሰፊ የማስተባበር (የማስተዳደር) ሥራ ይሰራሉ፡፡ በተለይ በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙ ታዋቂ የዓይን ሐኪሞችን በብዛት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ እና የህክምና እርዳታ እንዲያደርጉ አስተባብረዋል፡፡ ፊዚሺያንስ አክሮስ ቦርደር ከተሰኘ አለም አቀፍ ድርጅት ጋር በመሆን በዓለም ላይ በአይን ህክምና ታዋቂ ሐኪሞችን በበጎ ፈቃደኝነት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ በማስተባበር 80 ሺህ ገደማ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የአይን ህሙማን እንዲታከሙ አድርገዋል፡፡ በሕክምናው ከ20ሺህ በላይ አይነ-ብርሃናቸውን ተከልለው የነበሩ ኢትዮጵያውያን ማየት ችለዋል፡፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼን በዚህ ሥራ በመርዳቴ እርካታዬ ወሰን የለውም ይላሉ፡፡

**በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት በጤና ባለሞያዎች ብዙ ጊዜ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?**

ጥያቄ:- የጤና ባለሞያ ነኝ የሙያ ፍቃድ ለማግኘትና እና በስራው ለመመዝገብ በመጀመሪያ ምን ምን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አለብኝ?

መልስ:-
* የትምህርት ማስረጃ (ዲግሪ፣ ዲፕሎማ፣ ሰርተፍኬት፣ ትራንስክሪፕት ሲቀርብ
* አግባብ ያለው የስራ ልምድ (በስራ ላይ ለቆዩ ባለሞያዎች) ወይም የወጪ መጋራት ላለባቸው ባለሞያዎች አገልግሎታቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ ከሚሰሩበት ጤና ቢሮ/ ተቋም ሲፃፍ
* የጤና ምርመራ ሰርተፍኬት ሲይዙ
* የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ማስረጃ ሲቀርብ (ለውጪ ሀገር ዜጎች)
* የሙያ ፈቃድ ለውጪ ሀገር ዜጎችና ከዚህ በፊት የሙያ ፍቃድ ለወሰዱ ባለሙያዎች ሲቀርብ
* ሁለት የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ ሲቀርብ
* የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም

ጥያቄ:- ለጤና ባለሞያዎች letter of good standing የሚፃፈው ምን አይነት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው?

መልስ:-
* የማመልከቻ ደብዳቤ ሲቀርብ
* አግባብ ያለው የስራ ልምድና የስነ-ምግባር ሁኔታን የሚግልፅ ደብዳቤ ከሚሰራበት የጤና ተቋም አስጽፎ ሲቀርብ
* የሚፃፍለት ተቋም  አድራሻ ሲገለፅ
* የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም

ጥያቄ:- የመድሃኒት አስመጭና አከፋፋይ ድርጅቶች ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን የሚካሄደው እና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው እንዴት ነው?

መልስ:-
* በመመሪያው መሰረት አስፈላጊ መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ
* የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም

ጥያቄ:- የስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ቅድመ ፈቃድ ኢንስፔክሽን የሚካሄደው እና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው ምን አይነት ቅድመ-ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው?

መልስ:-
* በመመሪያው መሰረት አስፈላጊ መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ

ጥያቄ:- ለልዩ የጤና ማዕከላት ቅድመ ፈቃድ አንስፔክሽን የሚካሄደው እና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው ምን አይነት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው?

መልስ:-
* በመመሪያው መሰረት አስፈላጊ መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ

## የክልልና የፌዴራል የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች አስተባባሪዎች አድራሻ

| ተ.ቁ. | የክልልና የፌዴራል መ/ቤት | የመ/ቤት ስልክ |
|---|---|---|
| | | |
| 1 | የትግራይ ክልል የደያስፖ`ራ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት | 034 440 4280 |
| 2 | የአማራ ክልል የዳያስፖ`ራ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት | 058 220 0668 |
| 3 | የጋምቤላ ክልል የዳያስፖ`ራ ዴስክ | 047 551 1554 |
| 4 | የኦሮሚያ ክልል የዳያስፖ`ራ አስተባባሪ | 011 551 7658 |
| 5 | የቤንሻንጉል ጉሙዝ የዳያስፖ`ራ ተሳትፎ ጉዳዮች ፅ/ቤት | 057 775 0142 |
| 6 | ደቡብ ጋምቤላና የደቡብ ትብብር የዳያስፖ`ራ፣ፕሮቶኮል | 046 220 2407 |
| 7 | የሐረሪ ክልል የዳያስፖ`ራና የውጭ ግንኙነት አስተባበሪያ | 025 666 5264 |
| 8 | የሶማሌ ክልል ዳያስፖ`ራ ኤጀንሲ | 025 666 1800 |
| 11 | አዲስ አበባ የዳያፖ`ራ ዴስክ | 025 775 0056 |
| 12 | ድሬዳዋ ዳያስፖ`ራ ዴስክ | 011 158 0372 |
| 13 | አዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ቢሮ | 025 112 0070 |
| 14 | የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር | 011 157 8208 |
| 16 | የመ.ኮሙኒኬሽን | 011 553 7980 |
| 17 | ገቢችና ጉምሩክ | 011 552 9496 |
| 18 | ንግድ ሚ/ር | 011 551 8025 |
| 19 | ጤና ጥበቃ | 011 551 7011 |
| 20 | ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር | 011 515 9988 |
| 21 | ትምህርት ሚ/ር | 011 554 9704 |
| 22 | ፍትህ ሚ/ር | 011 554 1868 |
| 23 | ግብርና ሚ/ር | 011 515 6741 |
| 24 | ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ | 011 157 8204 |
| 25 | ባህልና ቱሪዝም | 011 515 7191 |
| 26 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | 011 554 1271 |
| 27 | ኢምግሬሽን | 011 551 9506 |
| 28 | ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ፓስፖ`ርት አወጣጥን በተመለከተ የሚሰራ | 011 155 0161 |

Content & Design by
Nathan Multimedia Production PLC
Tel. :- +251 11 8493813
Mobile :- +251 93 001 3078
E-mail: benyam_tesh@yahoo.com
Web Site :- www.nathanmultimedia.com

Federal Democratic Republic
of Ethiopia Ministry of Health







# The DIASPORA FOR HIS COUNTRY

## ETHIOPIAN DIASPORA IN THE HEALTH SECTOR













## Vision

**To see healthy, productive and prosperous Ethiopians.**

## Mission

**To reduce morbidity, mortality and disability and improve the health status of the Ethiopian people through providing a comprehensive package of promotive, preventive, curative, rehabilitative and regulating health services via a decentralized and democratized health system in collaboration with stakeholders.**

## Values

- **Community first**
- **Collaboration**
- **Commitment**
- **Change**
- **Trust**
- **Continued**
- **Professional development**

## Profile

- **Service Provider**
- **Service Purchaser**
- **Regulatory body**

**Address** :- Lideta Sub City Kebele 07/14 House No. 056
**P.O.Box** 1234 Addis Ababa, Ethiopia
**Tel** 011 551 7011, 011 551 7831
**Fax** 011 552 7033 **E-mail** moh@ethionet.et
**Web Site** www.moh.gov.et

# Message of the Ministry of Health

Ministry of Health



Dr. Amir Aman

State Ministry of health

There is something which everyone could do as regards the Diaspora. The government has created conducive atmosphere for Ethiopians and Ethiopian born persons living abroad to come home and take part in their country's developmental activities. Creating ideal condition doesn't mean that everything would be plain and straightforward. We do all we can as a government. Some Diaspora members returned home and have made impressive changes in spite of the challenges they faced. And those changes have opened our eyes to strengthen activities in this regard. Other members of the Diaspora have to follow the footprints of those who shone with success. The Diaspora played a tremendous role in the development of many countries around the world. In particular, they have made immense contribution in social, education and health sectors of those countries. Likewise, we expect a lot from the Diaspora. As a government our policy is open and our country is also theirs. We have created a good ground to enable all Ethiopians to work with us. Some are serving at our Ministry and the rest are providing voluntary service in the regional states. Seizing this opportunity I would like to call upon others to follow the pioneers to engage in the health sector as well as other developmental activities.

# Who is Diaspora?

The word Diaspora has no clear-cut definition at all places because it comprises the influx of people and various movements which has happened at different times in history. Thus, instead of considering the varied meanings of the word it is better to focus on the most common meaning of Diaspora which is widely used globally.

Modern Diaspora are those who migrate from their motherland and live in other countries forming own section or community less in number than the native people. This community has close spiritual and material connection or relationship with their homeland. Their stay in the second nation could be temporal or long lasting. The connection they have with their homeland has tremendous contribution to the economy

## Who is member of the Ethiopian Diaspora?

- Ethiopian diaspora is one who has Ethiopian citizenship and lived abroad at least for over a year.

## Who is Ethiopian born Diaspora?

- Ethiopian born diaspora is one who is Ethiopian in birth but who has citizenship of other country.





Ministry of Health

## Three key activities of the Ministry of Health:

1. Reducing  child mortality
2. Improving mothers health and reducing mortality
3. Reducing HIV, malaria and TB deaths through preventing and controlling communicable diseases
   venting and controlling communicable diseases

## Results scored through carrying out the 3 key activities

1. With regard to child mortality by reducing by 2/3rd Ethiopia has been able to achieve the set target two years before the deadline (2015).
2. In improving mother's health and reducing mortality Ethiopia has registered encouraging results. It reduced mortality by 63% in 2013. It has been reducing by 10 % until 2015 which enabled it to reach 79% by the deadline. And this is beyond the 75% plan set at the start.
3. The result that has been scored with regard to preventing and controlling communicable diseases is also encouraging.
   - Particularly, in reducing susceptibility to HIV it has been possible to achieve 90% compared to the previous time. The performance is beyond the MDGs and Ministry's target.
   - Susceptibility and deaths due to TB, malaria and other communicable diseases has also been reduced by over 60 %







# Remarkable achievements made in the health sector over the last two decades

Ministry of Health

- Before 1991 health institutions were 125, currently health institutions reached 3400.
- The number of colleges and universities offering health courses has shown drastic increment.
- The number of physicians is highly increasing.
- Accessibility and health coverage in urban and rural has greatly increased.



## Major challenges and the road ahead

- o Improving quality of health institutions
- o Enhancing service provision quality
- o Improving quality of health professionals



# Participation of Ethiopian Diaspora members

The government has adopted a policy enabling it to make use of resource, knowledge and skills of Ethiopian diaspora.

The document is known as the Federal Democratic Republic of Ethiopia Diaspora Policy. The policy has thoroughly looked into previous regulations and guidelines of other countries in the area. It has embraced various researches as input, utilized experiences of various countries and included comments and suggestions of Ethiopian diaspora.

- Upon the power vested in it the Ministry of Foreign affairs has set up a Directorate for Diaspora Affairs.
- The Directorate has broad structure; hence, it has set up offices of Diaspora Affairs in governmental offices and state towns.
- The Ministry and the Directorate have carried out a number of impressive activities within a short period of time.
- The Directorate has enabled many members of the Diaspora to invest in Ethiopia
- It has facilitated conditions for the diaspora to invest their knowledge and skills in their homeland while backing them to realize technology transfer.
- The Diaspora Affairs Directorate exchanges update information with the Ethiopian Diaspora through various media. It conducts various researches for the purpose of policy adoption.
- Informs Ethiopian Diaspora the preconditions needed to invest in home country.
- Encourages the establishment of the association of the Diaspora, assists them in celebrating Diaspora Day.

# Participation of the Ethiopian Diaspora in the Health Sector

Ministry of Health

The government has prepared encouraging environment for Ethiopian diaspora members interested to engage in the health sector.

Accordingly, it has been possible to engage about 1,700 diaspora members in the sector.



## Areas of investment in the health sector

- General and Special Hospitals
- General and Special clinics
- Clinical laboratories
- Diagnostic centers
- Pharmaceuticals centers
- Colleges and centers of health education and training







Dr. **Fekede Mengistu**

## Dr. Fekede Mengistu

**Ophthalmic Protection Centre** was established and owned by Dr. Fekede. He has 30 years of experience in the eye treatment and health service provision. He attended his first medical study in Ethiopia and pursued a graduate degree in Israel. He returned to his home country in1970 from Israel with the intention of serving his own people. When he returned home in early 1970s, there were only three ophthalmic specialists in the country. Since then he has been serving people in governmental and non-governmental institutions in various capacity. He believes that serving one's own people is a non-negotiable principle under any political system. He has provided ophthalmic related treatment to thousands of Ethiopians in different parts of the country. His firm commitment to return to homeland to serve his compatriots gave rise to exemplary achievements

**Saheleselasie Araya Higher Dental Clinic** was established and owned by Dr. Sahlsellasie Araya. He got medical training in the United States of America. He worked for over 25 years in USA. He also worked in his own clinic. Due to love to serve his people he returned to home country taking advantage of the positive environment created for the diaspora returnees by the Ethiopian government. He has built a great reputation in his profession in Ethiopia. He also has established a training center to take a step forward to standardize dental service in the country. Sahlesellasie Araya Dental service center has created job for many. Besides Ethiopian professionals the center has also employed foreign specialists.



Dr. Sahlesellasie Araya

Ministry of Health

**First Chiropractic Clinic** was established and owned by Dr. Selam Aklilu. She pursued medical training in North America. She lived there for over 27 years. She opened her own clinic and worked for 13 years in her stay. She seized the opportunity created by the Ethiopian government for the diaspora and returned home. Shortly after she established her chiropractic clinic many people began to look for her service. More than the money one could make, serving compatriots gives a lot of satisfaction, she says.



Dr. Selam Aklilu



Dr. Tewodros Melese

**Dr. Tewodros Melese** pursued medical training in USA. He worked in US for many years. He attended a specialized training on plastic surgery. He had great inspiration to promote the education he earned to his country. He returned home leaving behind better life in USA. In spite of the strange things he faced at home he managed to establish own clinic. He became famous in short period of time. He thinks that there are a lot of things which Diaspora members could contribute if they return to their homeland.

**Dr. Mesfin Tesfaye** is the founder and owner of Tesfamariam Higher clinic. He studied medical education in the USA. He returned home to serve his own people at home. He took advantage of the conducive situation created by the government for the Diaspora. In spite of the challenges he faced at the start he managed to realize his dream of establishing own clinic which brought him reputation.



Dr. Mesfin Tesfaye

**Merset Diagnostic Higher Clinic** is owned and run by Dr. Zewdu Terefework. He pursued his medical education in USA. He worked in many countries. He was successful in the countries he worked. He came home to provide service in the field of his specialization, Diagnostic treatment. He made use of the opportunity provided by the government to establish his diagnostic treatment center. Locally he introduced DNA and related treatment in search of which many people used to travel abroad. Presently, clinics and larger hospitals are clients of this center.



Dr. Zewdu Terefework



Ato Tamrat Bekele

**International Clinical Laboratories** has broad organizational structure which enabled it to create jobs for many citizens. The center was established with fund from international companies. Its Manager, Ato Tamrat Bekele, is one of the founders of the Centre. Ato Tamrat pursued health education abroad. He managed to realize his dream by establishing the center in Ethiopia. The center is mainly providing service to hospitals and international institutions. It has been able to win national quality award in his ten year journey. The center is opening main branches across the country. It has planned to open branches in South Sudan and Puntland as well. He advises Ethiopian Diaspora to have firm stand and take advantage of the conducive atmosphere created for the Diaspora in the country.



Dr. Mekonnen Hagos

**Medco Biomedical College** is the first private health college opened by Ethiopian Diaspora. It has become model to many private health colleges in the country. Dr. Mekonnen is the founder and owner of the college. He studied health education in Sweden and USA. He says that he worked for 21 years in USA and Europe on pharmaceuticals research. Realizing the gap in private health college and viable government policy in the area, he embarked on it. He was able to fix the challenges faced in the process of starting the new venture. Medco Biomedical College has created jobs for many teachers and administrative workers. It has contributed immensely to the country's health and treatment service by producing thousands of professionals.

He is the founder and owner of **Neyo Bio Medical Engineering** Medium Industry which produces and repairs medical equipment. It also assembles imported medical equipment. Ato Nega lived in the US for 15 years. He attended Bio Medical Engineering field in the United States. He served in various health institutions and hospitals in his profession. After identifying the gap prevailing in Bio Medical Engineering and the opportunity the government created for investors in his home country. He began to work in the area to fill the gap observed in hospitals. He managed to overcome the obstacles he faced thereby establishing a reputable industry which produces and repairs medical equipment. He has been able to manufacture locally some expensive facilities which used to be imported. His industry has repaired various precious equipment that were abandoned by hospitals.



Ato Nega Kebede

# Knowledge and skill transfer

## Migration of African intellectuals to USA, Europe

Ministry of Health

According to some researches, about 25-30% African intellectuals live in Europe and America. Every year about 20-30 thousand intellectuals migrate to industrialized countries of Europe and America from developing countries. About 30-40% Ethiopians who left their country and live in USA and Europe are those who have pursued postgraduate degree.

According to World Health Organization report, close to 175 million (2.9% of world population) people live in foreign country. Out of this figure only 65 million play active role in the economy.

## Health professionals influx

Health professionals, among others, move from one country to another. Various communicable diseases such as HIV/AIDS, malaria, TB and others are affecting people in Africa while they are fleeing their countries. Though many diseases in Africa are those which could be cured easily, many people are still suffering owing to the shortage of health professionals.

## Efforts made to repatriate the professionals

- Governments in Africa are providing encouraging incentives to health professionals more than ever. To this end, they are working with the theme: From Brain Drain to Brain Gain.
- The governments have set strategies which could bring the health professionals to their homeland.
- The main task in this area is to bind together stakeholders in the health sector and African health professionals in Diaspora.
- The strategies include adoption of viable policies in the area of previously forgotten opportunities and areas.
- Enhancing exchange of best medical practices is another key duty of the Diaspora members. It also includes the need for encouraging foreign partners to provide support in knowledge and skills transfer.

# Members of the Ethiopian Diaspora in Knowledge and Skills Transfer

Ethiopians in the Diaspora have long been making tremendous contributions to strengthen Ethiopia's health system through targeted knowledge and skills transfer. A number of organizations are implementing programs that enable Ethiopian health professionals in the Diaspora to provide voluntary service in support of their homeland. One such organization, the American International Health Alliance (AIHA), has been working with the FMOH since 2006 to recruit and place skilled professionals in long-term volunteer placements designed to deliver onsite technical assistance and mentoring to build sustainable institutional and human resource capacity at host sites throughout Ethiopia.

## The Role of Non-governmental Institutions in the Area of Knowledge and Skills Transfer

**AIHA's HIV/AIDS Twinning Center and Volunteer Healthcare Corps in Ethiopia**

• AIHA currently manages seven capacity-building twinning partnerships in Ethiopia, along with a very successful Volunteer Healthcare Corps (VHC) initiative that targets Ethiopian health and allied professionals in the Diaspora.

• AIHA works closely with the FMOH to ensure that programs are designed and implemented in alignment with national strategies and priorities.

• Through institutional twinning, AIHA facilitates the open and ongoing transfer of knowledge, and skills, and professional experiences that benefit partner institutions (e.g., universities, hospitals, clinics, NGOs, etc.) in both Ethiopia and America.

• One of AIHA's main objectives in Ethiopia and other countries where they work is, to contribute to efforts to reverse "brain drain" and support "brain gain". One of our strategies for accomplishing this is by engaging skilled Ethiopians in the Diaspora, tapping into their wealth of knowledge and expertise as a way to effectively support priority initiatives of the FMOH.

# AIHA Twinning Partnerships in Ethiopia

**AIHA has been creating partnerships to build health system capacity in Ethiopia since 2006. Examples include:**

- **Debre Berhan Referral Hospital and Elmhurst Hospital Center (New York) -** this partnership resulted in the FMOH recognizing Debre Berhan Hospital as a national benchmark hospital for organizational structures and service provision.
- **Addis Ababa University School of Medicine and the University of Wisconsin School of Medicine (Madison) -** this partnership has pioneered the education and practice of adult and pediatric emergency medicine in Ethiopia, creating a new sub-specialty for physicians and nurses, as well as spearheading training for paramedics and other first responders. As a result, Ethiopia has become the third country in all of Africa to start such training.
- **Jimma University Institute of Technology and Tegbar-Id Polytechnic College and Rice University and Texas Children's Hospital (Houston) -** this partnership has provided the technical support needed to help the Ethiopian partner institutions become national model training facilities for biomedical engineering and technology.
- **Addis Ababa University School of Pharmacy and Howard University School of Pharmacy (Washington, DC)** - this partnership worked to transform pharmacy education and practice across Ethiopia, shifting the paradigm to a more clinical focus that effectively integrates pharmacists into clinical care teams in keeping with international best practices for optimal patient care.

## AIHA's Role in Engaging and Supporting the Diaspora

- AIHA is an international nonprofit organization, headquartered in Washington, DC, with office in Addis Ababa & other African countries .
- AIHA recruits volunteers - in this case skilled Ethiopian professionals in the Diaspora - and places them in long-term assignments (3 months up to 2 years) across Ethiopia, where they work with local staff to rapidly and effectively assess capacity development needs and transfer knowledge and skills based on those needs.
- AIHA provides ongoing in-country support to their volunteers and covers international and in some cases domestic transportation, housing allowance, and a modest cost of living stipend.

**AIHA's Twinning Center would like to take this opportunity to call for all Ethiopians in the Diaspora, along with friends of Ethiopia, to contact them and learn more about how to contribute to the FMOH's initiative of improving healthcare in Ethiopia!**

## Alliance for Brain Gain and Innovative Development Ethiopia (ABIDE)

- Non-governmental indigenous organization.
- ABIDE strives to maximize brain gain through developing and strengthening institutional mechanisms and processes needed to coordinate and facilitate strong links and partnerships between local institutions and the Diaspora.
- Works jointly with various governmental and non-governmental institutions.
- Conducts researches on demands of local health professionals.
- Works closely with the Ministries of Education, Foreign Affairs and Ministry of Health to provide professional support in Ethiopia.

## Voluntary Service Overseas Ethiopia (VSO-E)

It is an international non-governmental organization whose main duty is working towards poverty reduction through providing support in education and health sectors.

- It is known with its principle 'Sharing skills, improving lives'.
- It recruits voluntary health and education professionals from around the world and brings to Ethiopia.
- It is carrying out a wide range of activities to facilitate conditions for Ethiopian diaspora to come on voluntary basis to share their knowledge and skills.
- The head quarter in Canada is in charge of recruiting and sending the volunteers to Ethiopia.
- The organization is open both to Ethiopian diaspora and foreign partners of Ethiopia interested to provide service in the health and education sectors in Ethiopia.

## Dr. Firew Lemma:


Dr. Firew Lemma

He is a health professional who lived and worked abroad for many years. Currently, he is a senior advisor at the Ministry of Health mainly in the areas of food system policy formulation, strategy and implementation. Though he came for three month voluntary service, he has extended his stay to the fourth year. He is happy with serving his country. He urges other Ethiopian diaspora to come and serve own people at least for a brief period.

## Dr. Wondwosen Eshetu:

He is a health professional who has provided voluntary service at various international organizations. Currently he is providing consultancy service to the Ministry of Health and various medical schools. He has now returned to his country for good. He is happy with that. He believes that Ethiopian health professionals in diaspora would get enormous satisfaction if they do the same.


Dr. Wondwosen Eshetu

## W/ro Kokeb Berhanu:



W/ro Kokeb Berhanu

She studied IT and Public Administration. She lived and worked for 14 years in USA. Kokeb came to provide short term voluntary service but she permanently settled here. She has worked on voluntary basis at the Ministry of Health and the Federal HIV/AIDS Prevention and Control Office. She says that she is delighted with serving at governmental offices.



W/ro Seble Nebiyeleul

## W/ro Seble Nebiyeleul:

She is well versed in health center administration. She worked as hospital administrator in USA. She lived for over 28 years in US. Since recently she is providing voluntary service in Ethiopia particularly in child care. She is delighted with it. Her organization, International Fund for Africa, provides medical equipment support to hospitals.





Teacher Yasin Rajiu

## Teacher Yasin Rajiu:

He is qualified in public relation and business management. Through his organization, Albasar Foundation, he contacts, brings and administers health professionals from various partners of Ethiopia and provides health service at home. In particular, he enabled many professionals and ophthalmic professionals to come to Ethiopia and provide free service. In collaboration with Physicians across Border, he facilitated the coming of ophthalmic physicians from around the world and provided treatment for more than 80,000 patients. Due to the service, close to 20,000 Ethiopians have regained their sight. I am very pleased with helping my people in such a manner.

What are the questions frequently asked by health professionals with regard to the Ethiopian Authority of Food and Drug Health care Administration and Supervision?

Q:- I am a health professional what preconditions am I supposed to fulfill to get professional license and get registered in the profession?

A:-* By bringing certificates of qualifications -- degree, diploma or certificate and transcript

* For those who have been working at home valid work experience or a letter of cost sharing clearance is needed from their health institution
  * medical certificate
  * English language proficiency (for foreigners)
  * when professional license of foreign professionals is presented to those who already have professional license
  * two passport size photographs
  * service fee paid

Q:- Under what preconditions letter of good standing is issued to health professionals?

A:- * Letter of application
  * letter from one's institution stating work experience and person's conduct and discipline
  * address of institution needs to be stated clearly

Q:- How is pre-license inspection done to drug importers and distributors and competence assessment issued?

A:- * when all credentials are fulfilled in accordance with the regulation
  * when service fee is complete

Q:- Under what circumstances pre-license inspection is done to specialized hospitals drug importers and distributors and competence assessment issued?

A:- * When all credentials are fulfilled in accordance with the regulation

Q:- How is pre-license inspection done to various centers and competence assessment issued?

A:- * when all credentials are fulfilled in accordance with the regulation

| Addresses of State and Federal Diaspora Participation Coordination | | |
|---|---|---|
| No. | State and Federal Office | Office telephone |
| | | |
| 1 | Tigray State Diaspora Coordination Office | 034 440 4280 |
| 2 | Amhara State Diaspora Affairs Directorate | 058 220 0668 |
| 3 | Gambella State Diaspora Desk | 047 551 1554 |
| 4 | Oromia State Diaspora State Coordination Office | 011 551 7658 |
| 5 | Benshangul Gumuz Diaspora Participation Affairs Office | 057 775 0142 |
| 6 | South Gambella and South Cooperation Diaspora Protocol | 046 220 2407 |
| 7 | Harari State Diaspora and Foreign Relations Coordination | 025 666 5264 |
| 8 | Somali State Diaspora Agency | 025 666 1800 |
| 9 | Addis Ababa Diaspora Desk | 025 775 0056 |
| 10 | Dire Dawa | 011 158 0372 |
| 11 | Addis Ababa Investment | 025 112 0070 |
| 12 | Ministry of Labour and Social Affairs | 011 157 8208 |
| 13 | Government Communication | 011 553 7980 |
| 14 | Customs and Revenue | 011 552 9496 |
| 15 | Civil Service Ministry | 011 515 9988 |
| 16 | Education Ministry | 011 554 9704 |
| 17 | Agriculture Ministry | 011 515 6741 |
| 18 | Investment Agency | 011 157 8204 |
| 19 | Culture and Tourism | 011 515 7191 |
| 20 | Commercial Bank of Ethiopia | 011 554 1271 |
| 21 | Immigration | 011 551 9506 |

This document was made possible through the generous support of the American people with funding from the US President's Emergency Plan for AIDS Relief (PEPFAR) and the US Centers for Disease Control and Prevention (CDC) in Ethiopia; in support of the Federal Ministry of Health (FMOH) through the Diaspora program which is managed by the American International Health Alliance's HIV/AIDS Twinning Center, that is funded by the US Department of Health and Human Services, Health Resources and Services Administration (HRSA).

Content & Design by
Nathan Multimedia Production PLC
Tel. :- +251 11 8493813
Mobile :- +251 93 001 3078
E-mail: benyam_tesh@yahoo.com
Web Site :- www.nathanmultimedia.com